# ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የሚያበቃው፡
# ሃይማኖትና ምግባር፡
# ከፍሬያማ ጸጋውና ከድል አክሊሉ ጋር!

በዚህ የጎዋ ሰሌዳችን ላይ የሠፈሩትን መጻሕፍትና መልእክታት ካነበቡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ውስጥ፡ በዚሁ የጎዋ አውታር አማካይነት፡ ከእኛ ጋር የእ-ጦማር ልውውጦችን ያካኼዱና እያካኼዱ ያሉ፡ ብዙዎች ናቸው። ከዚህ የተነሣ፡ በመካከላችን፡ የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ ግንኙነቶች እየተመሠረቱ፡ እየራሳቸውን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እስከማብቃት የደረሱት ግለሰቦችና ቤተሰቦች ቊጥር ምን ያህል እንደኾነ፡ በትክክል የሚያውቀው፡ ስማቸውን፡ በእግዚአብሔር የሕይወት መጽሓፍ የሚመዘግበው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

ይህን፡ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ፡ አንባቢዎቻችን ታውቁትና ትገነዘቡት ዘንድ፡ እውነታውን አብራርቶ የሚያስረዳውና በገሃድ የሚያሳየው፡ አንዱ፡ ያደረግነው የእ-ጦማር ልውውጥ፡ በጥያቄና መልስ መድረካችን ላይ የወጣ ቢኾንም፡ የተለየ ትኵረት ተሰጥቶት ሊነበብ የሚገባው መስሎ ስለታየን፡ ይህንኑ ልውውጥ፡ ለዓይነት ያህል፡ እነሆ፡ ከዚህ ቀጥሎ አቅርበንላችኋልና፡ ተመልከቱት!

---

## Email from Woizero Fikerte፡

Ethiopian Greetings Dear Nibure-Id Ermias!

Before clicking on the “send” button after composing and attaching this letter, I strongly felt like commenting on it; especially, how I was feeling when I wrote it.

On Saturday (Tahsas 17, 2002 E.C), I sat down in front of my computer to retrieve the email exchanges I made with you so far, with special intention to read MY letters. I didn’t have them because I used to save only your responses. Fortunately, however, I got all my letters in my sent box. So, I started reading them, together with your responses for each.

I realized that I initially started by talking about alerting and Ethiopianizing OTHERS through curriculum, multicultural education, publications … what have you! (Poor me! I even talked about the white people a lot.) But recently, I am faced with a new challenge-Ethiopianizing myself; and I found it harder than I thought. The shift of focus from OTHERS to MYSELF was not drastic though. It took 3+ years, and it isn’t completed yet..

With this in mind, I continued composing the letter I started earlier (which eventually became the attached letter). For a reason that I don't know, it was very hard for me to write this letter.. I felt the questions I wrote were redundant while at the same time I felt it was radical for me and my husband. I think I know the answers. But, I wanted to walk slowly with my husband. However, I don't deny that there is something slow in my brain, too.

Something is compelling me to write you some things, I don't know if you have to know them. But, I think I must write them, so that the 5 day labor to compose this letter finally comes to an end.

I am more convinced now than before that I must respond to my Lord's call to assure Him that I am an Ethiopian who believes in the Holy Covenant. This is because of three main reasons:

a. During Felseta (of 2001), I presented my question to the Lord and His Virgin Mother in the clearest way I could (I am not a good practitioner of a prayer and fasting by the way). Here is what I said: "Dear Lord, 4 years ago, when I graduated and got a job, I came to your house and prayed 'where do you want me to go? Show me the way!' and on my way home, I saw those books (of Nibure-Id) in the nearby stationary and the moment I read the titles, a bell rang loudly in my head. Was that you? Or was that just a coincidence?" and I tried my best to keep asking this question during Tsome-Tsige, and I am doing that now for Tsome-Nebiyat; and a bell kept ringing louder and louder in my head, which triggered my discussion with my husband with increased level of intensity on the issue of the Holy Covenant Ethiopian Identity. When I tried to "write the bell sound down," it gave birth to the main point of the attached letter.

b. As the bell sound got louder, especially the past few months, I realized that I was cured from a negative, redundant and destructive thought which lived with me since I was a little girl; and that couldn't stop despite my every effort including "tsebel" and "si'elet". Now that mentality is not absorbing or redundant anymore..

c. It has now been a year since I started teaching kids in the "gelelitegna" church I and my husband attend; and several kids were initially "mute" and disengaged; but, after I adopted your books to their level with some pictorial illustrations, the kids started to be engaged in the lesson very deeply, and the impact was so profound that some kids urged their parents not to take them to protestant or Catholic or any other Churches. When asked why not, they said "because they never tell us about Ethiopia." Again, a bell rang in my head, "was it that much fundamental?!

No wonder why I felt betrayed by my family, my teachers, my government and the whole adult when I read from a newspaper, as if I was an outsider, that St. George was on the battle of Adowa. Now they are feeling the same way."

So, "neger beSost Yitsenal" endilu, yihen sost neger ayiche teredahu…

**ከወ/ሮ ፍቅርተ ከተጻፈው፡ ከዚህ እ-ጦማር ጋር አባሪ ኾኖ የተላከው ዋና ደብዳቤ፡**

**ይድረስ፡- ለንቡረ እድ ኤርምያስ ወልደ-ኢየሱስ።**

**በኀዋ ሰሌዳዎ የጥያቄና መልስ ክፍል ላይ፡ የቅርቦቹን የእኔን እ-ጦማሮችና የእርስዎን ምላሾች እንዳወጡዋቸው ሳይ፡ በጣም ደንግጬ ነበር፡፡ ከእኔ ስም ጀምሮ በቀጥታ ሰዎችንና ማኅበራትን የሚመለከቱት ስሞች ተለውጠው እንደወጡ ሳይ ግን፡ ለጊዜው ተንፈስ አልኩና በራሴ ሳቅሁ፡፡ "እስኪ አሁን፡ እ-ጦማሮቹ በሙሉ፡ እንደነበሩ፡ ምንም ለውጥ ሳይደረግባቸው ወጥተው ቢኾን ምን ይፈጠር ነበር?" ብዬ ራሴን ስጠይቅ፡ ስለእግዚአብሔር እውነት የተማርኩትን ኹሉ በድፍረት ለመመስከር፡ ወይም ያደረግኹትን ኹሉ በግልጥ ለማድረግ፡ ገና ድፍረት የሌለኝ መኾኔን፡ ተገነዘብኩ፤ ድፍረት ቢኖረኝ ኖሮማ ምን ያስደነግጠኛል?**

**ነገር ግን፡ ከዚህ የበለጠ አንገብጋቢ የኾኑና ድፍረትን የሚጠይቁ፥ እኔ ግን፡ በፍርሓት መንፈስ ያለፍኳቸው ነገሮች፡ በፊትም እንደነበሩ ኹሉ፡ እስከአሁንም አሉ፤ ቢኾንም፡ "ፍርሓት ከመሰናክልነቱ በጊዜው ይወገዳል!" ብዬ በማመን ራሴን አጽናንቼዋለሁ፡፡**

**በሚያዚያ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፩ ዓ.ም. በጻፉልኝ እ-ጦማር ላይ፡ በወንጌል፡ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸው ቃላት መካከል፡ በተለይም፡ ሰው፡ በእውነት የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ከፈለገ፡ ከገዛ ወገኖቹና ቤተሰቦቹ ጭምር፡ ጨክኖ፡ ራሱን እና/ወይም አካሄዱን እስከመለየትና መስቀሉን እስከመሸከም ሊያደርሰው የሚችል ቁርጠኛ ፈቃደኝነት ሊኖረው እንደሚገባ የሚያመለክቱትን ቃላት በመጥቀስ፡ "በዚህ የሃይማኖትና የምግባር አቋምሽ ምክንያት አንቺንም ቤተሰብሽንም የሚጠብቃችሁ ጽዋ፡ ከዚህና ከቀረው የጌታ መለኮታዊ መመሪያና ማስጠንቀቂያ ውጪ ሊኾን፡ ከቶ አይችልም" በማለት የጻፉልኝን ቃል ያስታውሱታል፡፡**

ምንም እንኳ በዚያ ደረጃ የሚያሳስብ ነገር ገና ያልገጠመኝ ቢኾንም፡ እስካሁን የተመለከትኩዋቸው ፍንጮች ግን፡ በርግጥም አስቸጋሪ የኾነ ኹኔታ፡ እኔንም ኾነ ቤተሰቤን ሊገጥም እንደሚችል በበቂ የሚያስረዱ ኾነው አግኝቼያቸዋለሁ፡፡ ከፍንጮቹ መካከል አንዱና ዋነኛው፡ በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችንና በሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶች ውስጥ አብረን ከምንሳተፍ ብዙዎች አባቶች፥ እናቶች፥ ወንድሞችና እኅቶች ጋር፡ የአስተሳሰብና የአካሄድ ልዩነታችን፡ ቢያንስ ለእኔ፡ በጣም እየጎላብኝና ዘርፈ-ብዙ እየኾነብኝ መምጣቱ ነው፡፡

ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያት፡ የዚህ የአካሄድና የአስተሳሰብ ልዩነት ጉዳይ እየጎላ ሲመጣ፡ እኔና ባለቤቴ ምን ማድረግ እንደሚገባን በምንማከርበት ወቅት፡ ራሳችንን በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት ውስጥ በግልጥ እንድናስገኘውና አቋማችንን፡ በቅድሚያ ለራሳችን እንድናረጋግጥ፥ ለዚህም፡ እርስዎ በደብዳቤዎ ላይ፡ "አንደኛው ማማረጫ ነው!" ብለው እንደጠቀሱልኝ፡ ከውግዘቱ ነጻ ከኾነ ካህን (ለጊዜው፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ ከእርስዎ) ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል እንድንጸና ለባለቤቴ በማማክርበት ወቅት፡ ከዚያ በኋላ፡ በቀጣይነት ሊኖረን ስለሚገባው አካሄድ፡ ለኹለታችንም፡ በተለይ ለእርሱ፡ እምብዛም ግልጽ ስላልኾነ፡ ጥቂት ጥያቄዎችን ለመሰንዘር ፈልጌ ነው፡፡

የመጀመርያው ጥያቄዬ፡ በመጻሕፍቶችዎ ውስጥ በዝርዝር ተገልጦ እንደሚገኘው፡ አንድ ሰው በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት ውስጥ ለመኾኑ ለራሱና ለእግዚአብሔር ማረጋገጥ ሲፈልግ፡ የቃል ኪዳን ጸሎቶቹን በይፋ አንብቦ ወይም ጸልዮ፡ ቅዱስ ቁርባን ይቀበላል፤ እና፡ ይህን ለማድረግ፡ እኔና ባለቤቴ በመጨረሻ ተስማምተን ስንወስን፡ የምስክርነቱን ሥርዓት የምንፈጽመው የት ነው? እርስዎ፡ ብዙውን ጊዜ የሚኖሩት በኢትዮጵያ እንደኾነና፡ አልፎ አልፎ በቤተሰብ ምክንያት ወይም ለበዓላት ብቻ ወደአሜሪካ እንደሚመጡ፡ ከዚህ ቀደም ባደረግናቸው የእ-ጦማር ልውውጦች፡ በሚገባ ገልጸውልኛል፡፡ ይህን አገልግሎት የሚያበረክት፡ ከቤተሰቦችዎ ወይም ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት አባላት መካከል፡ ሌላ ካህን በአሜሪካ አለ? ወይስ እርስዎ ብቻ ነዎት ይህን አገልግሎት የሚያበረክቱት? የውጭው አገልግሎትዎስ፡ መደበኛ የኾነ መርሐ-ግብር አለው? ለምሳሌ፡- በበዓል፥ በሱባዔ ወይም በሌላ ጊዜ?

ኹለተኛውና ዋናው ጥያቄዬ (ጥያቄያችን) ደግሞ፡ "ከቃል ኪዳን ምስክርነትና ከቅዱስ ቁርባን <u>በኋላ</u> ያለው አኗኗር፡ በተለይ በኢትዮጵያ፡ ምን መምሰል አለበት?" የሚል ነው፡፡

ይህን ዘርዘር ሳደርገው:- እኔም ኾንኩ ባለቤቴ፡ እግዚአብሔር በሰላም ያድርሰንና፡ ዕቅዳችን፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ፡ ወደኢትዮጵያ ተመልሰን ኑሮአችንን በዚያ ለማድረግ ስለኾነ፡ ከዚያ በኋላ በመንፈሳዊ ኑሮም ኾነ አገልግሎት ላይ የሚኖረን ሱታፌ ምን መምሰል እንዳለበትና ከመለኮታዊው ውግዘት ነፃ ኾኖ ለመኖር ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን የበለጠ ለመረዳት ነው፡ የፈለግነው፡፡

በርግጥ፡ በዋነኛነት፡ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗንና፡ "ኢትዮጵያዊነት" ማለትም ሰባቱን ቃል ኪዳናት አምኖ በመቀበል በቃልም ኾነ በሥራ መመስከር፡ ታላቁና ብቸኛው ጥንቃቄ መኾኑን፡ እኔ በበኩሌ፡ ከልቤ አምኜበታለሁ፡፡ ነገር ግን፡ ትንሽ ያልገባን ገጽታ፡ በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ በተግባር የሚገለጡ አገልግሎቶችን የተመለከተ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ በሌሎች የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በግልም ኾነ በማኅበር ጸሎት፥ በበዓላት፥ በአገልግሎት (ማስተማር፥ መዘመር፥ በጎ አድራጎት፥ ወይም ሌላ)፥ በጽዋ መርሐ-ግብር፥ በገዳማት ደግሞ፡ ጠበል በመጠመቅ፥ ሱባዔ በመያዝና በመሳሰሉት መንፈሳዊ ተግባራት ላይ መሳተፍ፡ የውግዘቱ ተካፋይ ያደርጋል ወይ? ይበልጡንም ደግሞ፡ ከቤተሰቦቻችን መካከል ገና ያልተጠመቁ እንዳሉ፡ በማንኛውም ቤተክርስቲያን ወስዶ ምሥጢረ ጥምቀትን ማስፈጸም፥ የንስሓ አባት ማስያዝና ማስቀረብ የመሳሰሉት አገልግሎቶች፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖት በሚገኝ ሰው ፈጽመው መደረግ የሌለባቸው ናቸው ወይ?

<u>መልሱ "አዎን" ከኾነ፡ ለኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡ በተለይ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን በማበርከት ረገድ፡ በኢትዮጵያ አገልግሎቱ የሚሰጠው በማን ነው? በእርስዎ ብቻ ነው? ወይስ ሌሎች አገልጋዮችም በኢትዮጵያ አሉ?</u>

ለጥያቄዎቼ፡ እንደተለመደው፡ እውነተኛና ከመንፈስ ቅዱስ የኾነውን ምላሽ እንደሚሰጡኝ እየተማመንሁ፡ ይህን እ-ጦማር፡ በጎዋ ሰሌዳዎ ላይ ሊያወጡት፡ በርስዎ በኩል፡ አገልግሎትዎ የሚከተለውን ግልጽ አሠራር ለመጠበቅ አስፈላጊ ኾኖ ከተገኘ፡ ቢያወጡት ሙሉ ፈቃዴ መኾኑን ለማረጋገጥ እወዳለሁ፡፡

## ለዚህ የወ/ሮ ፍቅርተ እ-ጦማር የተሰጠ መልስ:-

በታኅሣሥ ፲፱ ቀን፥ ፳፻፪ ዓ. ም. ጽፈው የላኩልኝ እ-ጦማርዎ፡ ከነአባሪዎቹ ደርሰውኝ፡ በኹለንተናዊ ደስታ ተመለከትኋቸው። ቸሩ እግዚአብሔርንም ከነእናቱ፡ በመንፈሳዊ ሓሤት ኾኜ አመሰገንሁት። በዚህ ኹኔታ ማመስገኔ፡ ያለምክንያት አልነበረም፤ እ-ጦማርዎ የያዘውን ዜና መስማት፡ በተለይ፡ ለእኔና ለመሰሎቼ፡ ምሥራች ስለኾነ ነው።

ይልቁንም፡ እ-ጦማርዎን ጨርሰው ጽፈው፡ ወደእኔ ያስተላለፉበት ጊዜ፡ ሰሞኑ፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የትስብእቱ ምሥራች የተነገረበት ሲኾን፡ ዕለቱ ደግሞ፡ አብሣሪው ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ ሠለስቱ ደቂቅ የተባሉትን ስደተኞ የእስራኤል ወጣቶች፡ ከባቢሎን እሳት ያዳነበት ከመኾኑ ጋር፡ ይኸው ርግበ ኖኅ የኾነው ዜናዎ፡ ለእኔ ደርሶኝ ያነበብሁበት፡ የዛሬው፡ የታኅሣሥ ፳፪ ቀን፡ "ብሥራተ ገብርኤል" ተብሎ፡ የዚሁ ባለምሥራች መልአክ ብሥራት (ምሥራች)፡ ዓመታዊ በዓሉ የሚከበርበት መኾኑ፡ መለኮታዊ ተአምር እንጂ፡ ሌሎች፡ "አጋጣሚ" የሚሉት አለመኾኑን፡ እኛ፡ በሃይማኖት ከማረጋገጥ፡ ወደኋላ አንልም፤ ይህም፡ እርስዎ፡ በእ-ጦማርዎ ውስጥ ከጠቃቀሷቸው፡ ተአምራታውያን የሕፃንነት ትዝታዎችዎና የቅርብ ጊዜ የአንክሮ ትርኢቶችዎ ቅጥያ ለመኾኑ ሊጠረጠር አይቻልም።

ገና ከመነሻው፡ የገድል ጉዞዎን የጀመሩት፡ እውነተኛው የሃይማኖትና የአምልኮ አቋምዎ ባስገኘልዎ፡ በጠባቢቱ የመንፈስ ቅዱስ መንገድ መኾኑን፡ ዛሬ፡ ወደበቁበት፡ የምሥራቹ የድል አክሊል ለመድረስ የተጠቀሙባቸው፡ እነዚያ ሃይማኖታውያን ምግባራት፡ አረጋግጠው የሚያሳዩ፡ አጥጋቢ ማስረጃዎች ናቸው። ለመግቢያ ያህል፡ ይህን ካልሁ፡ አኹን፡ ወደዋናዎቹ ኹለት የእ-ጦማር ጥያቄዎችዎ አምርቼ፡ ምላሹን አቀርብልዎታለሁ።

፩ኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን መሠረት፡ እርስዎና ባለቤትዎ፡ ኹለታችሁም፡ ገና፡ ከየእናቶቻችሁ ማሕፀን እንደወጣችሁ፡ እንደሥርዓታችን፡ እርሳቸው፡ በ፹ ቀናቸው፥ እርስዎ፡ በ፵ ቀንዎ፡ በተጠመቃችሁና በክርስትና መጠሪያችሁ ተሰይማችሁ፡ በሕይወት መጽሐፍ በተመዘገባችሁ ጊዜ፥ ቀጥሎ፡ ቅዱሱን ቅብዓት (ሜሮን) በተቀባችሁና ማተባችሁን ባሠራችሁ ጊዜ፥ ከዚያም፡ በቆረባችሁ፡ ማለትም፡ የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን በተቀበላችሁ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ልጆች እና የመንግሥቱ ወራሾች፥ እንዲሁም፡ ካህናቱ (አገልጋዮቹ) እና ምሉካኑ (ንጉሥና ንግሥት) ኾናችኋል።

ይህ፡ በመንፈስ ቅዱስ ያገኛችሁት፡ የቅድስና ጸጋና በረከት፥ ሞገስና ባለሟልነት፥ ክብርና ማዕርግ፥ መብትና ሥልጣን፡ ከዚያች ቅጽበት፥ ሰዓትና ዕለት ጀምሮ፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፥ ለዘለዓለምም፡ በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ታትሟል፥ ጸንቷል፥ ጸድቋል። በተለይም፡ እናንተ፡ ጋብቻችሁን የፈጸማችሁት፡ በሥርዓተ ምሥጢረ ተክሊልና በቅዱስ ቁርባን ከኾነ፡ በዚያ ሥርዓት፡ ይህ ማንነታችሁ፡ በአዋጅ፡ ይፋ ወጥቶ ተገልጧል፥ ታይቷል፥ ታውቋልም ማለት ነው።

በዚህ ረገድ፡ “በእውነትና በመንፈስ መመለክን ከሚፈልገውና ከሚወድደው፡ ከእግዚአብሔር” ካገኛችሁትና ከተቀባችሁበት፡ ከዚህ ክህነታችሁ ጋር፡ እየራሳችሁ፡ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ ስለመኾናችሁ፥ ደግሞም፡ ዛሬ የምንገኝበትን ኹኔታ የመሰለ፡ የስደት፡ ማለትም፡ የሃይማኖት ፈተናና መከራ ከመድረሱ የተነሣ፡ ከመለኮታዊው ውግዘት ነጻ የኾኑ እውነተኞች ካህናትና ትክክለኛውን አምልኮ ልናካኺድባቸው የምንችልባቸው አብያተ መቅደሶች በሚታጡበት ጊዜ፡ ያ፡ የዓፀባ (የችግር) ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ፡ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መንበርነት፡ ቤታችን፡ ቤተ ክርስቲያን ኾኖ ሊያገለግለን የሚበቃ ስለመኾኑ፥ እንዲሁም፡ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእያንዳንዳችን፡ አማናዊውና ብቸኛው አናዛዥ ካህናችንና ሊቀ ካህናታችን ስለመኾኑ፡ እነዚህንና እነዚህን የመሰሉትን የመንፈስ ቅዱስ እውነታዎች፡ ቀደም ብለው በወጡት ዕትሞቻችንና የጎዋ ሰሌዳ ጽሑፎቻችን፥ ከእኔም ጋር በተለዋወጥናቸው ደብዳቤዎችና ኢ-ጦማሮች በሚበቃ እንደተረዳችሁት አምናለሁ።

እንግዴህ፡ ይህ እውነታ፡ የሃይማኖታችን አካል ከኾነ፡ የቃል ኪዳን ምስክርነቱን፡ እርስዎና ባለቤትዎ፡ በቤታችሁ የጸሎት ቦታ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ፊት፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ፡ አብራችሁ ወይም፡ በተናጠል ቆማችሁ፡ ለቃል ኪዳን ፈጣሪያችንና አምላካችን፡ ለእግዚአብሔር፡ ለአንድነቱ፡ ፩ ጊዜ፥ ለሦስትነቱ፡ ፫ ጊዜ፥ ለእመቤታችን ድንግል ማርያም፡ ፩ ጊዜ፥ ለልጇ፡ ለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል፡ ፩ ጊዜ ሰግዳችሁ፡ ያለመዘግየት፡ በማናቸውም አመቺ ቀንና ሰዓት፡ በእየራሳችሁ የምትፈጽሙት እንጂ፡ ለዚህ ሥርዓት ብላችሁ፡ እኔ ዘንድ መምጣት፥ ወይም፡ የእኔን በአጠገባችሁ መገኘትን መጠበቅ፥ ወይም፡ ኢትዮጵያ ድረስ መጓዝ፡ የሚያስፈልጋችሁ አይደለም።

የቃል ኪዳን ምስክርነቱን ሥርዓት በምትፈጽሙበት ጊዜ፡ በመጨረሻ፡ ልታደርጉት የሚያስፈልገው ተጣማጅ ተግባር፡ ከዚህ የሚከተለው ነው፡- እርሱም፡ በኖኅ አማካይነት፡ በቀስተ ደመናው፡ የአረንጓዴ ብጫ ቀይ ኅብረ ቀለማት፡ ከፈጣሪያችን የተቀበልነው፡ የ፪ኛው ቃል ኪዳንና የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን ምልክት የኾነውን ማተብ፡ በየአንገታችሁ ላይ የማሠሩ ባህላችን ነው።

እነዚህ ሦስት ቀለማት ያላቸውን ፈትሎች (ወይም ክሮች) በአንድነት በመግመድ፡ ማተቡን፡ ራሳችሁ አሰናድታችሁ፥ በሥርዓቱም ላይ ጸልያችሁበትና ባርካችሁት፡ በየአንገታችሁ ልታደርጉት ትችላላችሁ። ከቸገራችሁም፡ በደብዳቤ ቤት በኩል፡ እኔ፡ ከዚህ፡ ልልክላችሁ አያስቸግረኝም።

ስማችሁን፡ በጸሎት የምናነሣበትን ደረጃ ለማስተካከልና ለዚህ ሰማያዊ ክብር በመብቃታችሁ፡ ምስጋናችንን፡ ከሓሤት ጋር፡ ለቸሩ አምላካችንና ለቅድስት እናቱ ለማቅረብ፡ ሥርዓቱን መፈጸማችሁን ብታስታውቁኝ ደስ ይለናል።

ቅዱስ ቍርባንን በሚመለከት፡ አኹንም እየተቀበላችሁ ስለኾናችሁ፥ በዚሁም የምትቀጥሉበት በመኾናችሁ፡ ይኸው ምግባራችሁ በቂ ነውና፡ ለዚህ ብላችሁ፡ ወዲያ ወዲህ በመዘዋወር የምትደክሙበት፥ ወይም፡ የቆይታ ጊዜን የምትወስዱበት፡ ምንም ዓይነት ምክንያት ሊኖር አይችልም።

ይህን የተቀደሰ ምግባር ለመፈጸም ከፈለጋችሁ ደግሞ፡ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ኾኖ፡ ከእኔ ጋር በዓይነ ሥጋ ለመገናኘት እስክንችል ድረስ፡ ከዚህ ቀደም፡ ባመለከትሁዎ፡ በአንዱ ማማረጫ መጠቀም ይቻላል፤

ይኸውም፡ አኹን ካላችሁበት፡ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሰበካ ቤተ ክርስቲያን ኼዳችሁ፡ ቅዱስ ቍርባንን መቀበል ነው፤ አለዚያ፡ ይህን ማድረግ የሚከብዳችሁና የማትፈልጉ ከኾነ፥ እኔ፡ ወደእናንተ፥ ወይም፡ እናንተ፡ ወደእኔ መጥታችሁ፡ ሥርዓቱን ለመፈጸም የምንችልበትን ዘዴ መፈለግና መንገዱን ማዘጋጀት ይቻላል።

እዚህ ላይ፡ በዚህ በኩል፡ ልንረሳቸው የማይገቡ፡ ቍም ነገሮች አሉ፤ እነዚህም፡ የእናንተን የሥልጣነ ክህነት ባለጸጋነትና የሥጋ ወደሙን መንፈሳዊነት የሚያረጋግጡት፡ የእግዚአብሔር እውነታዎች ናቸው፤ ይህም ማለት፡ ቅዱስ ቍርባንን፡ የመቀበሉ ፍጹም ፈቃደኝነታችሁና ቍርጥ ውሳኔያችሁ፡ በእናንተ በኩል፡ በእውነት ካለ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ መልአኩን ልኮ በሚፈጽመው መለኮታዊ ምሥጢር፡ እንደተቀበላችሁ የሚያስቆጥረው፡ የእግዚአብሔር የቸርነት ሥራው ነው፤ ይህም፡ "አዎን! ይህ፡ በእግዚአብሔር፡ ሊኾን ይችላል!" ብላችሁ፡ በውስጥ ኅሊናችሁ በምትሰጡት ሃይማኖታዊ ማረጋገጫ፡ እውን የሚኾን ነው።

፪ኛውና ዋናው ጥያቄያችሁ የኾነውን ቁም ነገር ለመመለስ፡ እዚህ ላይ፡ ልንገነዘበው የሚገባን መሠረታዊ ጉዳይ ስላለ፡ በቅድሚያ፡ ያንን ማመልከት የሚያስፈልገኝ ይኾናል።

ይህም፡ ለኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አቋም፡ ግንድ ከኾነው፡ ከቤተ ሕዝቡ፡ ከሠረፁት፡ ከኹለቱ ዓበይት ቅርንጫፎች መካከል፡ (ኹለተኛው፡ ቤተ ምልክናው ሲኾን፡) አንደኛዋ፡ ቤተ ክህነት መኾኗንና ዛሬ ያለችው፡ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡ እንዲህ እንደመኾኗ፡ "የእኛ ናት እኮ!" የሚለውን ሃይማኖታዊ እውነታ፡ እንደገና ማመልከት ነው፤ ታዲያ፡ እንዲያ ካልኾነ፡ እናንተ እና እኛ፡ መስቀሉን ተሸክመን፡ ዛሬ፡ እንዲህ፡ በገድል ጽናት የምንቃተልላት፡ ለምንድር ነው? እርሷን፡ ከክፋት ኃይላትና ከባዕዳን ተጻራሪዎቿ፡ የግዞት ቀንበር፡ ነጻ ልናወጣት አይደለምን? ለዚህ መኾኑንማ፡ ምንጊዜም ልንዘነጋው አይገባም።

በመምህርነቱና በአርአያነቱ፡ በታማኝነት የምንከተለው፡ መለኮታዊው መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚህ ረገድ፡ ራሱ ፈጽሞት፥ እኛንም እንድናደርግ የሰጠንን መመሪያ፡ አውቀነው፡ ይኸው፡ እየሠራንበት እንገኛለን።

እርሱኮ፡ በዘመኑ የነበረችውን፡ ራሷን፡ የአይሁድን ቤተ ክህነት (ቤተ መቅደስ)፡ "የአባቴ ቤት፡ የጸሎት ቤት እንጂ፡ የሌቦች ዋሻ አይደለችም!" ብሎ፡ በርኵሰት የማሰነ ኹለንተናዋን፡ በግዘፍ ጠርራን፡ በንጽሕና ሸለማት፥ በመጨረሻም፡ በሕማማተ መስቀሉና በፈሰሰው ደሙ ዋጅቶ፡ በቅድስና አስጌጣት እንጂ፡ ያችን ትቶ፡ ሌላ ቤተ ክህነት፥ ሌላ ቤተ መቅደስ እኮ አላቋቋመም።

የዛሬዪቱ፡ የእኛዋ ቤተ ክህነትም እኮ ያቺው ናት! ቀድሞ፡ በዘመነ ብሉይ፡ በኪዳነ ልቦና፡ በኢየሩሳሌም፡ በእነመልከ ጼዴቅ ተመሥርታና በመካከሉ፡ በኪዳነ ኦሪት፡ በእነሰሎሞን ታንፃ፡ በእውነተኞች ታማኞች ካህናቷ ስትገለገል የቆየችው እኮ ናት፡ የእኛዋ ቤተ ክህነት!

ከዚያም፡ በየትውልዱና በየዘመናቱ በሚነሡ፡ በእነዚያ አንገተ ደንዳኖች አይሁድ ዐመፅ፥ ክህደትና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአት ጠንቅ እየማሰነች፡ የኋላ ኋላ፡ በባቢሎናውያን የቅጣት ሠይፍ ፈርሳ ከመደምሰሷ በፊት፡ ታቦተ ጽዮን፡ በእግዚአብሔር ጥበባዊ ዕቅድ፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ከባለቃል ኪዳኑ እስራኤላዊ ንጉሥ፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከሰሎሞን በወለደችው፡ በቀዳማዊ ምኒልክ ምክንያት፡ ወደኢትዮጵያ ተመልሳ የመጣችው እኮ ናት፡ የእኛዋ ቤተ ክህነት!

በመጨረሻ፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በኢትዮጵያዊቷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያምና በኢትዮጵያዊው ልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ እስከተከሠተው ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ድረስ፡ በመጀመሪያዪቱና በጥንታዊቷ ኢትዮጵያዊት ቤተ መቅደስ የኖረችው እኮ ናት፡ የእኛዋ ቤተ ክህነት!

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰሰጡባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡” እያሉ በዘወትሩ፡ የሃይማኖት ጸሎታቸው የሚያወድሷት፥ “ቤተ መቅደስ”፥ ወይም፡ “ቤተ ክርስቲያን” እየተባለች፡ በተለያየ ስም የምትጠራው፥ በፍጥረት ልደትና ዛሬ፥ ወደፊትና ለዘለዓለምም፡ ሕያውት ኾና የምትቀጥለው፡ ያችው፡ አንዲቱ ቤተ ክህነት ናት እኮ፡ ይህችው፡ የእኛዪቱ ቤተ ክህነት።

ስለዚህ፡ ይህ የመከራና የፈተና ጊዜ አልፎ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ እንደገና፡ በገሃድና በይፋ ተገልጣ፡ በግዘፍ እስክትሰፍን ድረስ፥ ወይም፡ እውነተኞቹ ታማኞቿ አገልጋዮቿ ካህናት፡ ከነአብያተ ክርስቲያናቸው፡ እየራሳቸውን እየገለጡ እስኪቀርቡ ድረስ፡ በአገራችን ባሉትም ኾነ፥ በውጭ አህጉር ተበትነው በሚገኙ፡ የሰበካ፥ የደብርና የገዳም ካህናትና አብያተ ክርስቲያናት መገልገልንና ማገልገልን የሚከለክለን፡ አንዳችም ምክንያትና እክል ከቶ የለም።

በዚህ ረገድ፡ ልናደርገው የሚገባን፡ ዋናና ብቸኛ ጥንቃቄ ቢኖር፡ ከዚህ የሚከተለው ነው፡- እርሱም፡ ዓቅማችንና ሙያችን በሚፈቅድልን መጠንና መልክ፡ ለማናቸውም የእግዚአብሔር ፍጡር፡ አገልግሎታችንን በነጻ ከማበርከት በቀር፡ በማናቸውም ድርጅት፥ ማኅበር (የጽዋ ጭምር)፥ አቋም እና/ወይም አካል ውስጥ አባል ከመኾን፡ እየራሳችንን በጽኑ ተዓቅቦ መጠበቅ ነው፤ ማነኛውም ዓይነት አባልነት፡ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊም ቢኾን፡ ከቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ውጪ ሊያደርገንና ለመለኮታዊው ውግዘት ፍዳ ሊዳርገን ከሚችል፡ ጠንቀኛ ግዳጅ ጋር የተቆራኘ ከመኾን፡ በፍጹም ነጻ ሊኾን አይችልምና። የኋላ ኋላም፡ ከጥፋት አዘቅት ውስጥ ወድቆ፡ ከመጸጸት ይልቅ፡ አስቀድሞ መጠንቀቁና ራስን በተዓቅቦ ማዳኑ ይሻላል ማለት ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት፥ እንዲሁም፡ እናት አገራችን ኢትዮጵያ፡ በመላው ፍጥረተ ዓለም ላይ ሰፍነው የሚመሩና አጠቃልለው የሚያስተዳድሩ መኾናቸውን፡ እኛ፡ የቅዱስ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት አምነን፡ ይህንኑ ሃይማኖታችንን፡ ሕይወት አድርገን፡ ይኸው፡ እየኖርነው፥ በምግባራችንና በአገልግሎታችንም፡ ይኸው፡ በሥራ ላይ አውለን፡ ለመልካሙ ፍሬ እያበቃነው እንገኛለን።

የእግዚአብሔር የምንላት መንግሥት፡ በፍጻሜ ዘመን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትስብእት፡ በዘለዓለማዊ ሕያውነት፡ እውን የኾነችውና ገዝፋ የተገለጠችው ስትኾን፥ እናት አገራችን የምንላት ኢትዮጵያ ደግሞ፡ በድንግል ማርያም ፍጹም ሰብእና፡ በዘለዓለማዊ ሕያውነት እውን የኾነችውና ገዝፋ የተገለጠችው ናት፤ መላው ፍጥረተ ዓለም የምንለውም፡ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለው የአንድነት መለኮታዊ ቃልነቱና ሥልጣኑ የፈጠረው፡ በሰማይና በምድር የሚኖረው፡ ግዙፉ፡ ሥጋዊና ደማዊ፥ ረቂቁ፡ ነፍሳዊና መንፈሳዊም ፍጡር ኹሉ ነው።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከዚህ መለኮታዊ ባሕርይዋና አካሏ የተነሣ፡ በፍጥረተ ዓለሙ በሚኖሩ፡ በፍጡራን ላይ፡ ማለትም፡ በሰዎች ኾነ፥ በመናፍስት፡ በተቋቋሙ መንግሥታትና ግዝአታት (ግዛቶች)፥ ሕግጋትና ሥርዓታት ላይ፡ በበላይነትና በአጠቃላይነት የሠለጠነች ናት።

የእርሷ ባለመብቶችና ባለርስቶች ኾነው የሚተዳደሩባት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ደግሞ፡ ህልውናቸውና መመሪያቸው፣ ሕጋቸውና ሥርዓታቸው፡ ይህችው መለኮታዊቷ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለኾነች፡ በምድር ኾነ በጎዋ ጠፈር፥ በባሕር ኾነ በጥልቁ ጨለማ ተስፋፍተውና ተንሠራፍተው ካሉ፡ ከእነዚያ የፍጡራን መንግሥታትና ግዝአታት፥ ሕግጋትና ሥርዓታት በላይ፡ እነርሱ፡ ከፍ ብለውና በልጠው ይኖራሉ።

ስለዚህ ነው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዓለም ላይ፣ በማናቸውም አገርና ቦታ፥ በማናቸውም ሕዝብና ፍጡር ጋር፥ በማናቸውም ጊዜና ኹኔታ፣ ለራሳቸውም ኾነ፡ ለሌላው፡ ምንም ዓይነት ችግርን በማያስከትል አኳኋን፡ በሰላምና በደስታ መኖር የሚችሉት። የዚህም ምክንያት፡ ግልጽ ነው፡- እነርሱ የሚመሩባቸውና የሚተዳደሩባቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፥ ሕግና ሥርዓት፡ ከፍጡራን መንግሥታት፥ ሕግጋትና ሥርዓታት ይልቅ፡ እጅግ በመጠቀ ይዘት፡ የተሻሉና የበለጡ፥ የቀኑና የጠሩ፥ የሚጠቅሙና የሚያገለግሉ፥ የታመኑና የጸኑ ስለኾኑ ነው።

እርስዎም፡ በእ-ጦማርዎ ውስጥ፡ "በርግጥ፡ በዋነኛነት፡ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗንና "ኢትዮጵያዊነትን"፡ ማለትም፡ ሰባቱን ቃል ኪዳናት አምኖ በመቀበል፡ በቃልም ኾነ በሥራ መመስከር፡ ታላቁና ብቸኛው ጥንታቂ መኾኑን፡ እኔ በበኩሌ፡ ከልቤ አምኜበታለሁ።" ያሉት ቃል፡ በዚህ መልክ የተሠነዘረ ለመኾኑ፡ አጠቃቀስዎ፡ ራሱ፡ በቂ ማስረጃ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ "...በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ በተግባር የሚገለጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ፡ ...ለምሳሌ፡ በሌሎች የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት፡ በግልም ኾነ በማኅበር ጸሎት፥ በበዓላት፥ በአገልግሎት (ማስተማርን፥ መዘመርን፥ በጎ አድራጎትን፥ ወይም ሌላን)፥ ... በገዳማት ...፡ ጠበል በመጠመቅ፥ ሱባዔ በመያዝና በመሳሰሉት መንፈሳውያን ተግባራት ላይ መሳተፍን፡ ...ይበልጡንም ደግሞ፡ ከቤተሰቦቻችን መካከል ገና ያልተጠመቁ እንዳሉ፡ በማንኛውም ቤተክርስቲያን ወስዶ፡ ምሥጢረ ጥምቀትን ማስፈጸምን፥ የንስሓ አባት ማስያዝንና ማስቀረብን፡ የመሳሰሉት አገልግሎቶች"፡ ያለአንዳች ውልውል ሊደረጉ እንደሚቻል ማረጋገጡ አያዳግትም። እንዲያውም፡ የመንፈስ ቅዱስ፡ እሙን መሣሪያዎች በመኾን፡ ተልእኳችንን፡ በተግባር ላይ አውለን፡ ለጣፋጩ ፍሬ የምናበቃው፡ በውስጥ ኾነን፡ እንዲህ እያደረግን በመሳተፍ መኾኑ፡ በኹላችንም ዘንድ የሚታመንበትና ተቀባይነት ያለው አሠራር ነው።

ለጥያቄዎ የሚሰሰጠውን መልስ ለማሟላት ያህል፡ እንዲህ ቢባልም፡ ሊታወቁ የሚያስፈልጉ ኹለት ተዛማች ነገሮች እንዳሉ ማስተዋል ይገባል፤ እነዚህም፡ በቅድሚያ፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ ዛሬ፡ በሰዎች ይትበሃልና ሥርዓት፡ በውሱን መልክዓ ምድር ተከልላ በምትገኘው አገር ብቻ ሳይኾን፡ በመላው ፍጥረተ ዓለም ላይ የሰፈነችው፡ ሉዓላዊትና አጠቃላይ፥ ኹለንተናዊትና ረቂቅ፥ ምድራዊትና ሰማያዊት የኾነችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ሥራዋ፡ እጅግ ሰፊና አያሌ መኾኑ ነው፤ በተከታይ ደግሞ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚያ መለኮታዊ ሥራ በኩል፡ ያለብንን ተልእኮ፡ እያንዳንዳችን፡ በየግላችንም ኾነ፥ በኅብረት አከናውነን የመፈጸም ግዳጅ ያለብን መኾኑ ነው፤ ታዲያ! ያን ታላቅ ግዳጅ፡ ከግቡ ለማድረስ፡ "መቼ ትርፍ ጊዜ አግኝተን ነው፡ በሌላው የተግባር መስክ ውስጥ፡ ተሳትፎ ማድረግ የምንችለው?" በሚለው ጥያቄ ስለምንያዝ፡ በጥያቄዎ በኩል ያለው አፈጻጸም፡ እምብዛም፡ የሚያሳስበንና የሚያስቸግረን ሊኾን አይችልም።

እንግዲህ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጠሪነትና ሰብሳቢነት፡ ወደፊት፡ በአካለ ሥጋ ጭምር ተገናኝተን፡ "ለምናምንባትና ለምንኖርባት፥ ለምናገለግላትና ለምንጋደልላት፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ዛሬና ወደፊት፡ ልናደርግ የሚገባን፡ ምንድር ነው?" ብለን ለመመካከርና ለመወያየት፥ የምንስማማባቸውንም መርሃ ግብሮች፡ በሥራ ላይ አውለን ለመልካሙ ፍሬ ለማብቃት፡ የፈጣሪያችን ፈቃድ ኾኖ፡ መለኮታዊው ጥሪ እስኪደርሰን፡ በአዲሱ፡ "የምሥራች" መጽሓፍ መጨረሻ ላይ፡ የሠፈረውን ቃል በመጥቀስ፡ የዚህን የመልስ ጽሑፌን ሓተታ እደመድማለሁ።

“የቅዱስ እግዚአብሔር እና የቅድስት ኢትዮጵያ
ተወዳጆች ልጆች ሆይ!

“...በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ላይ ተመሥርቶ የጸናው፡ ሥጋዊውና ነፍሳዊው፥ መንፈሳዊውም ህልውናችሁ፡ በዘወትሩ ንስሓችሁ፡ ፍጹም ጤናማ፥ ከጥርጥርና ከውልውል፥ ከግመንታትና ከፍርኀት፥ ከጭንቀትና ከሥጋት የነጻ፡ መልካም ሕይወት ኾኖላችሁ እንደምትቀጥሉበት እናምናለን።

“ይልቁንም፡ እናንተ እና እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን ምክንያት፦ ስማችን፡ በእግዚአብሔር የሕይወት መጽሓፍ ውስጥ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተመዘገበ በመኾኑ፥ በመላው ዓለም በተዘረጋችውና በሰፈነችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በቀጥታ፡ ከፈጣሪያችንና ከቅድስት እናቱ ጋር፥ እንዲሁም፡ እርስ በእርሳችንና በመካከላችን የምናካኺደው ግንኙነትና ንግግር፥ ጥሪና ስብሰባ፡ እንደዓለማውያኑ፡ በሥጋ ሳይኾን፡ በመንፈስ መኾኑን፡ እናንተም፥ እኛም፡ በሃይማኖት ተቀብለን፥ በምግባር እየፈጸምነው ያለ ሥርዓታችን መኾኑን እንደተገነዘብነው እናውቃለን።

“ይህም ማለት፡ ‘እናንተ እና እኛ፡ የዘወትር ግንኙነታችንን የምናካኺደውና አንድነታችንን የምናጸናው፥ ተልእኳችንን የምንፈጽመውና ህልውናችንን የምንቀጥለውም፡ እንደሥጋውያኑ ባህል፡ በአባልነት በመመዝገብና መታወቂያ ደብተርን በመቀበል፥ የወር መዋጮንና የዓመት ግብርን በመክፈል፥ በትእዛዝ ተጠራርቶ፡ በአካል በመገናኘትና በመሰባሰብ፥ በቃል በመነጋገርና በጽሑፍ በመዋዋል ሳይኾን፥ ወይም፡ ይህ ኹሉ፡ የሰዎች ጠንቀኛ የአሠራር ፈሊጥ ሳያስፈልገን፥ በያለንበት እንዳለን ኾነን፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምላኳችን አማካይነት ብቻ፡ በየግላችንም ኾነ በማኅበር፡ በመንፈስ ቅዱስ በመገናኘትና በመነጋገር፥ በመጠራራትና በመሰባሰብ ነው!’ ማለት ነው።

“አዎን! ጥሪያችንንና ስብሰባችንን፥ ግንኙነታችንንና ንግግራችንን፡ በዚህ መልክ እያካኼድን፡ ኢትዮጵያዊቷን የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወታችንን እንኖራለን፤ አገልግሎታችንንም፡ በያለንበትና በየሙያችን፡ በመንፈስ ቅዱስ ማበርከትን እንቀጥላለን። ፈጣሪያችንና አምላካችን፥ መድኃኒታችንና መምህራችን፥ ካህን፡ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከቅድስት እናቱና እናታችን፥ መቅደስ ሃይማኖታችንና ገነት አገራችን፥ ታቦት ኪዳናችንና ጽዮን ንግሥታችን ድንግል ማርያም ጋር፡ ለግዙፉ ዓለም የሚገለጥበትንም፡ ዳግም ምጽአቱን እንጠባበቃለን።”

## ከወ/ሮ ፍቅርተ የተጻፈ የመጨረሻ እ-ጦማር፡-

ባለቤቴና እኔ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የሚያበቃውን፡ የቃል ኪዳን ምስክርነት የመስጠቱን ሥርዓት የፈጸምን መኾናችንን የምናስታውቅዎ፡ በልባዊ፡ የደስታ መንፈስ ነው።

## ለዚህ እ-ጦማር፡ ለወ/ሮ ፍቅርተ የተሰጠ መልስ፡-

ለዚህ ሰማያዊ ጸጋና ዘለዓለማዊ ክብር በመብቃታችሁ፡ ለቸሩ አምላካችንና ለቅድስት እናቱ ምስጋናችንን እያቀረብን እንገኛለን! እናንተንም፡ "እንኳን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ለዚህ፡ የሕይወት ልዕልና አበቃችሁ!" እያልን፡ ሓሤታችንን ከመግለጽ ጋር፡ ፍጹም ምርቃታችንን፡ ይኸው አበርክተንላችኋል!